# ግእዝ ሕያው ልሳን

# በቀላል ዘዴ

በ ዲያ ቆ ን ደ ሴ ቀ ለ ብ
ካ ቲ ት 1993 ዓ .ም
አ ዲስ አ በ ባ


www.debelo.org

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ**

## <u>የግእዝ ቋንቋ እድገት ከየት ወዴት ?</u>

መቼም ቢሆን እንዲት ሃገር የራሷ የሆነው ባህሏ /ሥርዓቷ/ የሚያኮራትና ማንነቷንም የሚያንጸባርቅ በመሆኑ ልትጠብቀውና ከትወልድ ወደ ትውልድ ልታስተላልፈው የባለቤትነት ግዴታዋ ነው፡፡ በመሆኑም ሀገራችን ኢትዮጵያን ለጥቁር ሕዝቦች መኩሪያ እንድትሆን ያደረጋት የልጆቿ ሀገር ወዳድነትና ጀግንነትን የተመላው ባህሏ ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት፣ የሥነ ፊደል ሀገር መሆኗም መጻሕፍተ ታሪክን ባነበቡ ሊቃውንት አንደበት ብቻ ሳይሆን በማዳመጥ ትውፊት /ርክክብ/ ለኅብረተሰቡ ኅቡእ ያልሆነ ነገር መሆኑ ነው፡፡

በተጨማሪም ሀገራችን ኢትዮጵያ የዘመናት ዑደት ስፍር ቀምራ የራሷን አኀዝ ያደላደለች አፍሪካዊት እመቤት ናት ብንል ጽልመት ሊጋርደው የማይችለው ገሀድ ነው፡፡

ይሁን እንጂ እኛ ልጆቿ የትናንቱን ለዛሬ ማበርከት ያልቻልን ይመስላል፡፡ ለዚህም ነው ትናንት የኢትዮጵያ መሠረተ ቋንቋ የነበረው የግእዝ ቋንቋ ከነበረበት የብሔራዊና የውል ቋንቋነት ይቅርና ዛሬ ዛሬ የትገባ ሊባል የሚያሳፍር ሆኗል፡፡ አበው ለብዙ ዘመናት ይህን ቋንቋ በዜማ ቤቱ፣ በቅኔ ቤቱ በመጻሕፍት ቤቱ እንዳልተጠቀመበት ሁሉ ዛሬ ግን የአበው ያለህ ብንል አይደለም መግባባት ይቅርና ገና ተማሪው እንኳን ከማለዳው "አኰ" /እሽ/ በማለት ፈንታ "አኬ" ቢል ይቀድመዋል፡፡ ይህ ግን #የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች፤ሳያሠኝ አይቀርም፡፡

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ታሪክ መረጃ ስነ ሐውልቶች የተሸከሙት የግእዝ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍ የሀገራችንን ጥንተ ታሪክ የሚያስረዳ መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል፡፡ የግእዝ ተፎካካሪ የነበረው የሳባዊያን ቋንቋም በግእዝ ተልቆ /ተበልጦ/ ግእዝ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሊቃውንት ኅብረተሰብ መግባቢያ ከመሆኑም አልፎ ከሀገር ውጭም ኢትዮጵያ ሀገረ ፊደል፣ ሀገረ አሚን መሆኗን ያስመሰከረ ልሳን ነበር፡፡ የሆነው ሆኖ ቀድሞ ከ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እየተጠናከረ መሄዱ በሚነገርለት በአማርኛ ቋንቋ መሆኑ ቀርቶ በቤተክርስቲያንና በተወሰነው የኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ እየተገደበ መጣ፡፡ እንዲያውም በተለይ በዘመነ ዓምደጽዮን /ከ 13*0* 7-1337 ዓ.ም./ የንጉሡ ገድል ሁሉ የሚጻፈው በተሰባበረ አማርኛ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተለውን ማየት ይቻላል፡፡

- ሐርልኛ ዓመደ ጽዮን



www.debelo.org

- መላለሸ የወሰን
- ወሀ እንዳመሰን መላላሸ የወሰን
- ከወጅ ዜብደናን ከገንዝጠጠን
- ምንቀረህ በወሠን ከድያ አምኖን

በተጨማሪም በዓፄ ይስሐቅ /ከ1407-1422 ዓ.ም./ ጊዜ ለንጉሡ የሚቀርቡት መወድሶች ከአማርኛው ላይ ያተኮሩ ይምስላሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል

- ገጽኸን ይስሐቄ ገጽ
- አርያም ይመስል አንቀጽ
- እሳት ይመስል ብቁጽ
- ከመ መደልውልጽሉጽ
- ገጹ እንዲያስደነግጽ
- እስራኤላዊ መደንግጽ
- ማን አየህ ገጽ በገጽ

እነዚህ ግጥሞች ግን እንደምናያቸው ሙሉ በሙሉ አማርኛ አልነበሩም፡፡ ለዚህም ነው ግዊዲ የተባለው የታሪክ ተመራማሪ “ግእዝ -አማርኛ” ጽሑፎች ብሎ የሚጠራቸው፡፡ በእርግጥ ከአማርኛው ላይ ግእዝ መደመር ለአሁኑ ትውልድም የቋንቋ ጣዕም የሥነ ጽሑፍ ቃና መሆኑ አወንታዊ ምላሽ አለው፡፡

ያም ሆኖ ግን ብዙ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የጽሕፈት ሥራቸውን ብራና ዳምጠው ቀለም በጥብጠው ይጠቀሙበት የነበረው በዚህ ቋንቋ መሆኑን አላገደውም፡፡ እንዲያውም በዘመነ ዘርዓያዕቆብ / 1426-1460 ዓ.ም./ መስፋፋት የነበረበት የሥነ ጽሑፍ እድገት ግእዙን የመጥኘ ያለ ነበር፡፡ በኋላም ቢሆን በዓፄ ሱስንዮስ /ከ1599-1624 ዓ.ም./ የሃይማኖት መለወጥ ምክንያት ጋር ተያይዞ ኢየሱሳውያን ( **Jesuites**)ጉልህ ችግር ደርሶባት የነበረችውን የሮማ (ስፔን) ካቶሊክ “ቤተክርስቲያን “ ተከታዮችን ቁጥር ለማበርከት ሲሉ በአማርኛ በመጻፍ ወረቀቶችን ለመበተን ቢሞክሩም የአንድ ባሕርይ አማኝ የሆነው አፄ ፋሲል /ከ 1624-1674ዓ.ም/ በመንገሥ የምእመናኑን ፍጹም ቀናዒነት ብሎም የኢየሱሳውያን ከኢትዮጵያ ምድር መውጣት ለልሳነ ግእዝ እንደገና መወለድ መስፋፋት ሆነለት፡፡ ብዙም መጻሕፍተ ግእዝ ተደረሱ፡፡ የቅኔ እድገትም ታየ፡፡ ከዓፄ ፋሲል በኋላም ነገሥታቱ ታላቅ ተሳትፎአቸውን አበርክተዋል፡፡ ስለሆነም ዓፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ/ ከ 1674-1699 ዓ.ም./ እና ሌሎችም ነገሥታት የማይጠፋ ስማቸውን በልቡናችን ቀረጸውአልፈዋል፡፡



www.debelo.org

ዳግመኛ የ16ኛው እና የ17ኛው ክፍለ ዘመናት ቁስል አልሽር ብሎ እንደገና በመሳፍንቱ ዘመን / ከ1777-1845 ዓ.ም/ ሀገሪቱ እርስ በርሷ በፖለቲካና በሃይማኖት ድልቅልቅ ስትዋጥ ሀገርን አንድ ማድረግ ይችል የነበረውን ነገረ-ሃይማኖት ለመረዳት ለመወሠን ሊቃውንቱ የግእዝን መጻሕፍት ማገላበጥ ግድ ሆነባቸው፡፡ የመነጋገሪያ /የመከራከሪያ/ ምሥጢራቸው የሆነው ቅኔም ለልሳነ ግእዝ መስፋፋት ጠቀመ፡፡ የአብነት ትምህርት ቤቶችም ተስፋፉ፡፡ ፍጹም የሆነ አንድነትም ታዬ፡፡ ዛሬስ የሃይማኖት ውዝግቡን የሚፈቱት የተኞቹ እውን መጻሕፍት ይሆኑ? በእርግጥ ዛሬ ግእዝ ያወቀው ሁሉ ነገረ ሃይማኖትን ተረዳ ማለት አይደለም፡፡ የሚማረውም ለሕይወት / ለፍቅር/ወይም ታሪክን ለማወቅ ላይሆን ይችላል፡፡ ነበርኩ ለማለትና ክዶ ለማስካድ እንዲመቸው የሚያስብም አይጠፋምና፡፡ በየዋህነት መማር ግን በአማናውያኑ አበውቀርቷል፡፡

እንግዲህ ለግእዝ ቋንቋ መዳከም ዐቢይ ምክንያት የአማርኛ መተካት ብቻ ሳይሆን ለቋንቋው የሚሰጠው ትኩረት መላላቱ የማያወላውል ምክንያት መሆኑ ነው፡፡ ዝም ብሎ ግን ቅርስ ቅርስ ማለት ብቻ ዋጋ የለውም፡፡ "ባዶ ብራና"ካልተነበበ ምን ሊሠራልን፡፡ በተጨማሪም መንግስትም ሆነ ማንኛውም አካል ግእዝ የቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ቅርስ መሆኑን ሊገነዘበው ይገባል፡፡ ቤተክህነትም ብትሆን የእነ ቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት እነ ድጓ፣ የዚቅ ቀለማት የእነ አባ ጊዮርጊስ መጻሕፍት ፣ እነ ሰዓታት በሌላ ቋንቋ ሊዜሙ"ይቻል"ይመስል ለግእዝ የሚሰጠው እንክብካቤ ያሳዝናል፡፡

ድሮ ድሮ የቆሎ ተማሪ ለምኖ ከፈዳውን፣ ቅሉን፣ ዳዊቱን አንግቦ የሚነጋገረው በዚህ ቋንቋ ነበር፡፡ እንደዛሬው ግን ለወደፊቱ አይደለም የሚነጋገር አባባሉን የሚያጠና / የሚቀጽል/፣ በደንብ ቅኔ የሚቀኝ ይቅርና ዳዊቱን አጣርቶ መድገምም ራሡ ያጠራጥራል፡፡ በእርግጥ በአንዳንድ የገጠር ቦታዎች የሚያስተምሩ ብዙ የሊቃውንት በረከቶች ቢኖሩም ነገ የሚተካው ግን ከግእዝ ይልቅ ጣሊያንኛ ፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ ብቻ ቢማር የሚያተርፈው ይመስለዋል፡፡ ይህ ግን "አባቱን አያውቅ አያቱን ይናፍቅ" ያሠኛል፡፡

ምንጭ መጻሕፍቱ በግእዝ የሆነው የሀገራችን ታሪክንስ አንባቢና ተርጓሚ ማን ይሆን? በዚህ እኮ ነው የሀገራችንን ታሪክ ለማወቅ የውጭ መጻሕፍት ላይ ጥገኛ የምንሆነው፡፡ አንባቢውና ተርጓሚው አላዋቂ ከሆነ ደግሞ ታሪክ ሀገር ቅድምና ሀገር በምልዑ ልብ የማይመሰከርበት ይመስላል፡፡ የሚገርመው ግን ብዙዎቹ የግእዝ መጽሐፎቻችን በፈረንጆቹ ላይ የማያልቅ ፍቅርን አሳድረውባቸው ቋንቋውን እስከ ሃምሳ ዓመት ድረስ ሲያጠኑ እኛ ግን "የሞተ ቋንቋ"አንለዋለን፡፡ ቋንቋው ሞተ ከማለት ግን



www.debelo.org

ታሪክ ሀገር ቅድምና ሀገር ሞተ ብንል ሳይሻል አይቀርም፡፡ ቢያንስ ቢያንስ በቤተክርስቲያን ለካህናቱ የምስጋናቸው አንደበት ግእዙ ነውና፡፡

እንግዲህ እናጠቃለውና ማንኛውም ክፍል /አካል/ ይህ ቋንቋ በጥንቱም ሆነ በአዲስ መልክ እንዲያድግ ጥረት ቢደረግ፤ የቅኔ መምህራኑም የግእዝ መምህራኑም ምንም እንኳን የኑሮ ችግር ቢኖርም ለራስ የሚስማማ ቦታን ከመምረጥ ለተማሪዎች የሚስማማ ቦታን መርጠ በገጠርም ቢሆን ማስተማር ይኖርባቸዋል፡፡ የቋንቋ ምሁራንም ለዚህ እድገት አስተዋጽዖ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ላይ የጥንቱ ሰዋስው **( Classical Grammar)** ይምጣልን፣ ይመለስልን፤ መካከለኛው ክፍለ ዘመን የጨለማ ዘመን ነውእያሉ እንዳማረሩት ሮማውያንና ግሪካውያን እንዳንሆን ያስፈራል፡፡ ስለሆነም ሥርወቃላትን ለመመርመር ሰወስውን ለመለየት ግእዝ ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡ ለዚህም ታላላቅ ደራሲያን ምስክሮች ናቸው፡፡ በተረፈ ግን ሁላችንም የታሪክ፣ የሀገር፣ የወገን፣ የቅርስ ባለአደራዎች መሆናችንን አንዘንጋ፤ እንቅልፉም ይብቃን፡፡

## <u>**አር ስ ት**</u>

1. **መራሕያን ምድብ ተውሳጠ ስሞች** /Pronouns/
    **1.1 ነባር አንቀጽ** /Verb to be/
    **1.2 ሥርዓተ ዐረፍተ ነገር በምሳሌ**
    **ጥያቄዎች**
2. **አመልካ** ቾ **ች**/Demonstratives/
    **ጥያቄዎችና** ሠ **ሳም** /Conversation/
3. **የግ**እ **ዝ ሥርዓተ ንባብ** /Pronunciation/
4. **የንባብ ዓይነቶች** /Reading Types/
5. **የንባብ ምልክቶች**
    **ትውውቅ**
6. **ግሥ አርዕስት** /Root verbs/

**ርባ ግስ** /Tense, Nouns and Adjective formation/

**የአንዳንድ ሕገ ወጥ ግሶች አካሄድ**

7. **አገባቦች** /Prepositions and Conjunctions/



www.debelo.org

ከግስ ሳይ የሚያርፉ አገባቦች

ከዘንድ አንቀጽ ሳይ የሚያርፉ አገባቦች ና ሌሎች ተስማሚ ቃሳት

ዘ፣ ንተ፣ ስ፣ስ

8. ተውሳከ ግስ /Adverb/

9. አሉ ዎች/Negation Maker/

ጥያቄዎችና ንግግር

10. አገናዛቢ አጸፋዎች /Possessive/ ና ስሞች/Nouns/

10.1 አገናዛቢ ተውሳጠ ስሞች/Possessive Pronouns/

10.2 የአንዳንድ አገናዛቢ አጸፋዎች ዝርዝርና የንዑስ አንቀጽ ዝርዝር

10.3 ተጠቃሽ ተውሳጠ ስም

10.4 «በ» በመራሕያን ሲረባ /Verb to have in pronoun/

10.5 ባለቤት ተውሳጠ ስም /Subjective pronouns/

10.6 ተሳቢ ተውሳጠ ስም /Objective Pronouns/

10.7 የሚያበዙ ፊደሳት

ጥያቄዎችና ንግግር

11. ገቢር ተገብሮ /Direct and indirect Object/

12. ቅጽል /Adjective/

ጥያቄዎችና ንግግር

13. ካልአይ አንቀጽ የትንቢት ወይም ያሁን ጊዜ

14. ት ዛዝ አንቀጽ

15. አር ስት ከንዑስ አንቀጽ ና ዘንድ አንቀጽ

16. ቦዝ አንቀጽ

ጥያቄዎች

17. የo ቢ ይ አንቀጽ ርባ መንገድ ና አምስቱ አዕማድ

ጥያቄዎች

18. «ይቤ» አለ

ጥያቄዎች

19. ነጠሳ ግስ፣ዘርና ነባር /Dictionary/ ና ቁጥሮች /Numerals/



www.debelo.org

1. **<u>መራሕያን ምድብ ተውሳጠ ስሞች /Pronoun/</u>**

**መራሕያን ማስት «መሪዎች» ማለት ሲሆን በግእዝ ቋንቋ አስር (10) የሚሆኑ ተውላጠ ስሞች (መራሕያን) አሉ፡፡**እነርሱም

**1. አነ........................................ ኔ**

**2. አንተ...................................አንተ**

**3. አንቲ ...................................አንቺ**

**4. ውእቱ................................ ሱ**

**5. ይእቲ.................................. ሷ**

**6. ንሕነ................................... ኛ**

**7. አንትሙ............................. ናንተ (ለቅርብ ወንዶች)**

**8. አንትን................................ ናንተ (ለቅርብ ሴቶች)**

**9. ወእቶሙ............................ ነዚያ (ለወንዶች)**

**10. ውእቶን............................. ነዚያ (ለሴቶች)**

**መራሕያን በዐረፍተ ነገር**

**ቀደሰ (ቀዳማይ አንቀጽ** Past tense) **=አመሰገነ**

**1. አነ ቀደስኩ 6 ንሕነ ቀደስነ**



www.debelo.org

| | |
|---|---|
| 2. አንተ ቀደስከ | 7 አንትሙ ቀደስክ ሙ |
| 3. አንቲ ቀደስ ኪ | 8 አንትን ቀደስክ ን |
| 4. ው ቱ ቀደሰ | 9 ወ ቶሙ ቀደሱ |
| 5. ይ ቲ ቀደሰ ት | 10 ወ ቶን ቀደሳ |

የግሱ የመጨረሻ ፊደል «ከ»ከሆነ ያንኑ መለየት አለብን፡፡ <u>ምሳሌ</u> ሰበ ከ ብሎ አነ ሰበኩ («ኩ»ይ ጠብቃል) ይሳል ንጂ ሰበኩ(«ኩ» ይላላል) አይልም ስለዚህ ማጥበቅ አለብን ማለት ነው፡፡

**1.1 <u>ነባር አንቀጽ (Verb to be)</u>**

ው ቱ= ነው፣ነበር፣ነሽ፣ነህ፣ናችሁ

ይ ቲ=ናት፣ነበረች

ው ቶሙ ( ሙንቱ)= ናቸ ው፣ነበሩ (ለወንዶች)

ወ ቶን (እ ማንቱ)=ናቸው፣ነበሩ (ለሴቶች)

<u>ምሳሌ</u>፣ አነ ው ቱ ፍኖተ ጽድቅ

አንቲ ው ቱ ተስፋሁ ለአዳም

አንተ ው ቱ ቤዛ ኩሉ ዓለም

ማርያም ይ ቲ መሠረተ ሕይወት

ጳውሎስ ወጴጥሮስ መምህራን ው ቶሙ

ሰሎሜ ወኤልሳቤጥ ቅዱሳት ው ቶን

**1.2 <u>ሥርዓተ ዐረፍተ ነገር በምሳሌ</u>**

ሕዝቅኤል ነቢይ

- ሕዝቅኤል ነቢይ ው ቱ
- ነቢይ ወ ቱ ሕዝቅኤል
- አኮ/አይደለም/ ነቢይ ሕዝቅኤል

«ው ቱ» ለሚለው አዎን አሉ ው «አኮ» ነው፡፡

የሚከተሉት ከ መራሕያን ከግሶች ጋር አዛምድ/አስተፃምር/

| | |
|---|---|
| 1. አንትን | ሀ ነበርኩ |
| 2. ው ቱ | ለ በሳዕነ |
| 3. አነ | ሐ ሖርኪ |
| 4. ው ቶን | መ ጸለዩ |
| 5. ይ ቲ | ሠ ቀተልክን |



www.debelo.org

ረ መጽአት

ሰ ኖምክሙ

ሸ ሖሬ

ቀ በልዐ

**ወልጥ ኀበ ልሳነ አምሃሬ (ወደ አማርኛ መልስ)**

1. ንሕነ ሖርነ ኀበ አ ክሱም ወሳስ
2. አንቲ ው ቱ መብርሃን
3. ማርያም ወለደት ወልዳ ዘበኩሬ
4. አንተ ወአነ ሰማእ ነ ቃለ ግዚአብሔር
5. እ ስመኑ/አነማን/ ው ቶሙ ዘሖሩ ኀበ ገዳመሲና

ወደ ግ ዝ መልስ /ወልጥ ኀበ ልሳነ ግ ዝ/

1. ወደ ጸሎት ቤት ሄድን፡ ፡
2. ኔ ነኝ ወደ ቤተክርስቲያን የሄድኩ፡ ፡ (ዘ=የ)
3. ነርሱ በሕብረት ተቀመጠ፡ ፡ (ኀቡረ=በኀብረት)
4. ቶማስ እና ጴጥሮስ መምህራን ናቸው ፡፡
5. ማርያም ድንግል የአሮን በተር (በትር=ብትር) ናት ፡፡
6. አንተ የክርስቶስን ወንጌል ሰበክ ሀ ፡፡
7. አንተ ሰባኪ አይደለህም፡ ፡

አስተካክለህ ጻፍ (ጹሑፍ በሥርዓተ ሰዋሰ ው)

ምሳሌ/ሐዘነ/ ማርያም አመተሰቅለ ክርስቶስ/ኀዘነት ማርያም አመተሰቅለ ክርስቶስ/

1. /ኖመ/አንተ ሳዕለ አራት/አልጋ/
2. /ሖረ/ አንትን ኀበ ደብረጽጌ
3. /ቆመ/ ማር ወማርያም ቅድመ ቤተ መቅደስ
4. /ኀደረ/ ፍሬ ጽድቅ ውስ ተ ቤተ አ ርድ ት/ተማሪዎች
5. /አርመመ/ ሚካኤል አመ ተሰቅለ አምላክ
6. /ተፈሥሀ/ ጻድቃን በ ግዚአብሔር

**2. <u>አመልካች /Demonstratives/</u>**

1. መራሕያን ያልናቸው ሁሉ አመልካቶች ሲሆኑ ይችላሉ፡፡ የሚ ወቁት ግን ንደሚከተለው በምሣሌ ቀርበዋል፤

   ተክለ ማርያም ሖረ ኀበ ደብረ መንክራት

   ው ቱ ሖረ ኀበ ደብረ ሊባኖስ

   ው ቱ ብ ሲ ሖረ ኀበ ደማስቆ

   ይ ቲ ወለት በልዐት ኀብስተ

ው ቶሙ ውሉድ አ መሩ ትርጓሜ መጻሕፍት

ው ቶን አንስት ሰገዳ ለ ግዚአብሔር አምላከ ኢትዮጵያ

ው ቶን አዋልድ በልዓ ህብስተ

ሙንቱ ውሉድ አንበቡ ወንጌለ ዮሐንስ

ማንቱ አንስት ሰገዳ ለ ግዚአብሔር አምላከ ኢትዮጵያ

ነጠላ ብዙ

ው ቱ ያ (that) ው ቶሙ( ሙንቱ) ነዚያ(those)

ይ ቲ ያቺ « ው ቶን( ማንቱ) «

- ነዚህ ሁሉ የሩቅ ወይም በሩ ሲና ያለን ነገር ያመለክ ሉ::

2. ዝንቲ ብ ሲ ሖረ ኀበ ኢየሩሳሌም ፣ ይህ ሰው ወደ ኢየሩሳ ሌም ሄደ: :

ዝ ብ ሲ ሖረ ኀበ ኢየሩሳሌም ፣

ዛቲ ብ ሲት መጽአት ም ደብረ ቦር ፣ ይቺ ሴትዮ ከደብረ ቦር መጣች: :

ዛ ብ ሲት መጽአት ም ደብረ ቦር ፣

ሉ ሰብ ሖሩ ኀበ ደብረ ከርቤ ግሽ ን ፣ ነዚህ ሰዎች ወደ ደብረ ከርቤ ሄዱ

ሳ ደናግል ቀዱሳት ማንቱ ፣ ነዚህ ደናግል ቅዱሳት ናቸው

ነጠላ ብዙ

ዝ፣ዝንቱ ይህ (This) ሉ ነዚህ(These)

ዛ ፣ ዛቲ ይች « ላ ነዚህ «

- ነዚህ ሁሉ የቅርብን ነገር ያመለክ ሉ::

3. ዝኩ መምህረ ቀኔ ው ቱ = ያ ሰው የቅኔ መምህር ነው ::

ዝንቱ «

ንትኩ ወለት ኀተ ሙሴ ይእቲ ያቺ ልጅ የሙሴ ህት ናት

ን ክቲ እ ስካለ ማርያም ይእቲ

ልኩ ሰብ ኢትዮጵያዊያን ው ቶሙ ነዚያ ሰዎች ኢትዮጵያውያን ናቸው::

ልክቱ

ልኮን ደናግል መጽአ ምገዳም ነዚያ ደናግል ከ ገዳም መጡ::

ልክቶን

ነጠላ ብዙ

ዝኩ፣ዝክቱ (ዝለኩ)=ያ (That) ልኩ ፣ ልክቱ = ነዚያ (Those)

ንትኩ ፣ ን ክቲ = ያቺ ልኮ ን፣ ልክቶን = ነዚያ

- ነዚህ ደግሞ ንደ ተራ ቁጥር አንድ የሩቅ ነገርን ያመለክ ሉ::

መልመጃ

አዛምድ (አስተፃምር ፣ አስተዛምድ)



www.debelo.org

1. ዝኩ
2. ው ቱ
3. አን ክቲ
4. ልክቱ
5. ይ ቲ
6. ሉ
7. ላ
8. ዝክቱ
9. ዝንቱ
10. ልከ ን
11. ልኩ
12. ሙንቱ
13. ዝ

አ. ሖረት
በ. ቀደስኪ
ረ. መጽአ
ደ. ነበሩ
ሀ. ሰገድኪ
ለ. ሖር ነ
ሐ. አንበብክሙ
መ. ቀደሰ
ሠ. ሐርክ ን

የሚከተሉትን ወደ ግ ዝ ተርጉም፤ ፈክር(ተርጉም) ኀበ ልሳነ ግእ ዝ

1. ያች ልጅ ቆንጆ ናት፡ ፡
2. ነዚያ ኤልሳቤጥና ማርያም ናቸው፡ ፡
3. ያ የወንጌል ተማሪ ነው፡ ፡
4. ይህ መጽሐፍ አዲስ ነው፡ ፡
5. ነዚህ የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸው፡ ፡

ሰላም

| | |
|---|---|
| ፎ ኀደርከ ኀየ | ግዚአብሔር ይሰ ባሕ |
| ( ንዴት አደርክ ወንድሜ) | ( ግዚአብሔር ይመስገን) |
| ትምህርት ፎ ው ቱ | ሠናይ ው ቱ |
| (ትምህርት ንዴት ነው) | (ጥሩ ነው) |
| ማእዜ ው ቱ ዘፈጸምክሙ ፈተናክሙ | ዘዮ ም ወርኀ |
| (መቼ ነው ፈተናችሁን የጨረሳችሁት) | (የዛሬ ወር) |
| በጽባሕ አይቴ ሖርከ ው ቱ ዘኢረክብኩከ | ኀበ ከኒሣ ቤተ ክርስቲያን |
| (በማለዳው ያላገኘሁህ የት ሄደህ ነው) | (ወደ ቤተክርስትያን) |
| አነ ሰ በጽባሕ ኀበ ቤተ ምግብ/ካፌ ው ቱ ዘሖርኩ | ግዚ ይባርከ ኩን ትጉህ |
| ( ኔስ በማለዳ ወደ ካፌ ነበር የሄድኩት) | (ጌ ይባርክህ ትጉህ ሁን) |
| ስምአኒ ዳዕሙ መኑ መሃረ ዮም | በይነ ነገረ ማርያም |


www.debelo.org

(ስማኝ ንጂ ዛሬ ማን አስተማረ) (ስለ ነገረ ማርያም)
በየነ ምንት ወ ሎቱ ስብሐት
(ስለምን) (አዎ ምስጋና ለሱ ይሁን)
ኩሉ ሰብአ ቤትከ፣ ምከ፣አቡከ፣አኀከ፣ዳኅና ው ቶሙ አሆ ለኩልነ
(ሁሉም ቤተሰቦችህ ደህና ናቸው) ( ሺ ለሁላችን)
በል ሠናይ ምሴት ጌሰም ንትራከብ
(በል መልካም ምሽት ነገ ንገናኝ)

## 3. የግእዝ ሥርዓተ ንባብ ( Pronounciation)

የግእዝ ሥርዓተ ንባብ ስምንት ናቸው ። ነርሱም፡ -

1. ማንሳት 5. ማናበብ
2. መጣል 6. አለማናበብ
3. ማጥበቅ 7. መዋጥ
4. ማላላት 8. መቁጠር ናቸው፡ ፡

1. ማንሳት ፡ ይህ ሥርዓተ ንባብ የቃሉ መጨረሻ ፊደል ሳድስ ከመሆን የተለየ ሆኖ ቃሉ በከፍተኛ ድምፅ የሚነገር ወይም የሚነበብ ማለት ነው ። ለዚህም ነው ሁሉም የግስ አይነቶች በከፍተኛ ድምፅ የተነበቡ ተነሽ ናቸው የሚባሉት ።

<u>ምሳሌ</u> ነበረ = ተቀመጠ

ሐበነ = ስጠን

ተዘከረኒ = አስ ውሰኝ

ው ቱ = ነው፣ነበር፣ ሱ፤ ናቸው ወዘተረፈ ።

አንስት ሖራ = ሴቶች ሔዱ

ይግበሮ = ይሥራው

ያጥምቆ = ያጥምቀው

2. መጣል (ተጣይ) ፡ ይህ ሥርዓተ ንባብ መጨረሻው ሳድስ ሆኖ የማይነሳ ማለት ነው ።

<u>ምሳሌ</u> ማርያም ፣ ሚካኤል፣ኢየሱስ ክርስቶስ፣ቤተ መንግሥት፣ቅድስት፣ መቅደስ ወዘተረፈ፡ ፡

3. ማጥበቅ ፡ ይህ ሥርዓተ ንባብ ከቃሉ ውስጥ የሚጠብቅ ፊደል ኖሮ ቃሉ ጠብቆ ንዲነበብ የሚያደርግ ነው ።

<u>ምሳሌ</u> ቀደሰ = አመሰገነ



www.debelo.org

ሰብሐ = አመሠገነ

ተዘከ ሮ = አስ ውሰው

ነጸረ = ተመለከተ

4. **ማላላት** ፡ ይህ ሥርዐተ ንባብ በቃሉ ውስጥ የሚጠብቅ ፊደል ሳይኖርና ንባቡም ላልቶ ሲነበብ ነው ።

ምሳሌ፡ ቀተለ = ገደለ

ነበረ= ተቀመጠ (ኖረ)

አምለ ከ =አ መለ ከ

ገብረ= ፈጠረ (ሠራ)

ፈጠረ= ፈጠረ (በአማርኛው ይጠብቃል)

5. **ማናበብ** ፡ ይህ ሥርዓተ ንባብ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ቃላት ንደ አንድ ሆነው ሲናበቡና ን፣ በን ወይም የን ሲያመጡ ነው ።

ምሳሌ ቤተክርስቲያን = የክርስቲያን ቤት

ቤተመቅደስ = የማመስ ገኛ ቤት

ትምህርተ ሃይማኖት =የሃይማኖት ትምህርት

ድንግለ ሙሴ

ሠሥራተ ገብርኤል

ዜና ሥላሴ

ውዳሴ ማርያም

ጥዑመ ልሳን

ወልደ ኢየሱስ

ተዋሕዶ ቃል

ዜና ቤተክርስቲያን

6. **አለማናበብ** ፡ ይህ ሥርዓተ ንባብ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ቃላት ራሳቸውን ችለው ሲነበቡ ወይም አንዱ ላንዱ አጎላማሽ ሲሆን ነው ።

ምሳሌ ቅዱስ አምላክ ይባላል ንጂ ቅዱሰ አምላክ አይባልም ።

ድንግል ማርያም

መጽአ ወል-ወልድ መጣ

ጳውሎስ ሐዋርያ



www.debelo.org

7. **መዋጥ** ፡ መዋጥ ማለት ከቃሉ ውስጥ ያለ ፊደል ንዲሁ ሳይጎላ በውስጠ ዋቂነት የሚነበብ ነው ። ከዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ፊደሉ በጽሑፍ ጊዜ ግን ሥርዓቱን ጠብቆ ይፃፋል ።

<u>ምሳሌ</u>፡ ወይን (wan)ተብሎ ንጂ ወይን (wayyin) ተብሎ አይነበብም ።

ድንግል- ከዚህ ላይ ን ተውጣለች

ገብር - ከዚህ ላይ ደግሞ ብ ተውጣለች። ሥለዚህ ገብር ባለሁለት ቀለም ነው ።

ኤልሳዕ ከዚህ ላይ ደግሞ ዕ ትዋጣለች።

ርኩስ ኩ ተውጣለች።

ከዚህ ላይ ብዙውን ጊዜ የሚዋጡት ቀለሞች ሲሆኑ መዋጥና አለመዋጣቸው ግን ንደ ንባቡና ንደትርጓሜው ይለያያል።

8. **መቁጠር** ፡ ይህ ሥርዓተ ንባብ በአንድ ቃል ውስጥ የሚገኙ ፊደላትን ያለምንም መዋጥ ማንበብ ማለት ነው።

<u>ምሳሌ</u>፡ ው ቱ ከሚለው ቃል ሁሉም ፊደላት ይነበባሉ ንጂ ሳድሰ ስለሆነች ብቻ የምትዋጥ አይደለችም።

ይ ቲ ፣መላ ክት፣ማርያም ፣ማዕከል ፣ ህት ፣ትማልም፣ ዮሐንስ ፣አ ጽ ፋር (ጥፍሮች) ስ አ ርት (ፀጉር) ፣ኤልያስ ፣ብሔር (ሀገር) ሙንቱ፣ ስብሐት፣ ሐዋርያት፣ መጻሕፍት ( ህ ትቆጠራለች)

ከ ነዚህ ሥርዓተ ንባቦች በተጨማሪ ሌሎችም አሉ።

<u>ለምሳሌ</u> ወዳቂና ሰያፍ

ሀ. **ወዳቂ**፡ - የምንለው ሥርዓተ ንባብ የቃሉ መጨረሻ ፊደል ካዕብ፣ ሳልስ ፣ ራብዕ ኀ ምስና ሳብዕ ሆኖ የማይነሳ ና ቃሉ ሲነበብ የመጨረሻውን ፊደል በመያዝ ንዲወድቅ የሚያደርግ የሥርዓተ ንባብ ዓይነት ነው።

<u>ምሳሌ</u> ኀቤሁ ወደሱ የዚህ ቃል የመጨረሻ ፊደል ሁ ካዕብ ሲሆን ወዳቂ ነው። ነገር ግን አንዳንድ ልዩነቶች ንዳሉ ማወቅ ያስፈልገናል።<u>ለምሳሌ</u> ው ቱ የሚለው ነባር አንቀጽ ተነሽ ንጂ ወዳቂ አይደለም። ንዲሁም ግሶች በትዕዛዝም ሆነ በሐላፊ ሲመጡ ወዳቂ ናቸው ማለት አንችልም።



www.debelo.org

**ለምሳሌ ሖሩ= ሔዱ ወይም ሑሩ= ሒዱ ብንልም ተነሸ ንጂ ወዳቂ አይደለም።**

**ለሣልስ ምሳሌ ከይሲ ብእሲ መዋቲ መሃሪ ወዘተረፈ ሲሆኑ ግስ ከሆነ ግን አይወድቅም፡ ፡**

**<u>ምሳሌ</u> ሰአሊ ለነ ቅድስት ከዚህ ላይ ሰአሊ የሚለው ቃል ወዳቂ አይደለም**

**ለራብዕ ምሳሌ** አንበሳ፣ ዜና፣ ወዘተረፈ ከዚህ ላይም በግስ የሚነገር ከሆነ አይወድቅም፡ ፡

<u>ለምሳሌ</u> እላ አንስት ሖራ /እነዚያ ሴቶች ሔዱ/ ከዚህ ላይ « ሖራ » የሚለው ይነሳል እንጂ አይወድቅም፡ ፡

ለኃምስ ምሳሌ ውዳሴ፣ ቅዳሴ፣ ይባቤ፣ ወዘተረፈ

ለሳብዕ ምሳሌ ዶርሆ/ዶሮ/፣ መንበሮ፣ ቀቲሎት/

ንዑስ አንቀጽ የሆኑት ሁሉ ወዳቂ ናቸው፡ ፡ በተጨማሪ ቦዝ አንቀጽ የሆኑ ወዳቂዎች እንዳሉም ማወቅ ያስፈልጋል፡ ፡ ነገርግን በግስ ትዕዛዝ ወይም ዘንድ አንቀጽ የሆኑት ሊነሱ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡ ፡

## 5. <u>የንባብ ምልክቶች</u>

- የማንሳት ምልክት
- የመጣል ምልክት
- የማጥበቅ ምልክት

አንዳንድ የግእዝ ግሶች የሚጠብቅ ድምፅ ሲኖራቸው ግማሾቹ የላቸውም፡ ፡

**ምሳሌ፣** ቀተለ --ገደለ፣ ቀደሰ --አመሰገነ

<u>ትውውቅ</u>

| | |
|---|---|
| ሰላም ለከ እኁየ | ወሰላም ለከ |
| (ሰላም ላንተ ይሁን ወንድሜ) | (ሰላም ላንተም ወንድሜ) |
| መኑ ስምከ እኁየ | ወልደ ገብርኤል ውእቱ ስምየ |
| (ስምህ ማን ነው ወንድሜ) | (ስሜ ወልደ ገብርኤል ነው) |
| ወመኑ ስመ አቡከ | ገ/ማርያም ውእቱ ስመ አቡየ |
| (ያባትህ ስም ማን ነው) | (ያባቴ ስም ገ/ማርያም ነው) |
| እስፍንቱ አዝማኒከ | እሥራ ወአሐዱ |
| (ዕድሜህ ስንት ነው) | (ሀያ አንድ) |
| እምአይቴ መጻእከ | እምጎጃም |
| (ከየት መጣህ ) | (ከጎጃም) |
| ግብር እፎ ውእቱ | ሚመ ኢይብል |



www.debelo.org

(ሥራ እንዴት ነው) (ምንም አይል)

እስኩ ነዓ ነሑር ጎበ ቤተ እግዚአብሔር ትፍስሕትየ ውእቱ

እስኪ ና ወደ ቤተክርስቲያን እንሂድ (ደስታዬ ነው)

ሕይወት እፎ ውእቱ ሠናይ ውእቱ

(ሕይወት እንዴት ነው) (ጥሩ ነው)

አሉ አብያጺከ ውእቶሙ እወ

(እነዚህ ጓደኞችህ ናቸው) (አዎ)

አይቲ ብሔሮሙ (ዝ እምሲዳሞ ወዝኩሰ እምወሎ)

(የት ነው ሀገራቸው) (ይህ ከሲዳሞ ነው ያ ደግሞ ከወሎ)

ትትሜሀርኑ ትምህርተ ዘመነ ዌ እወ እትሜሀር አነ ትምህርተ ዘመነ ዌ

(የዘመናዊ ትምህርት ትማራለህ) (አዎ የዘመናዊ ትምህርት እማራለሁ)

አይቴ ውእቱ ቤተ ትምህርትከ 6 ኪሎ ውእቱ ቤተ ትምህርትየ

(ትምህርት ቤትህ የት ነው) (6 ኪሎ ነው ትምህርት ቤቴ)

ስፍነ አመተ በጻሕከ ሰልሰ አመተ በጻሕኩ

(ስንተኛ ዓመት ደረስክ) (3 ዓመት ሆኖኛል)

ተአምርኑ ትምህርተ ሃይማኖትከ ወሀገርከ ምንት ውእቱ ትምህርተ ሀገርየ

(የሀይማኖትህ እና የሀገርህን ትምህርት ታውቃለህ) (የሀገሬ ትምህርት ምን ነው)

ንባብ፣ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ግእዝ፣ ቅኔ ይትበሀሉ ለእሉሰ አእምሮሙ ቀዲሙ

(ንባብ፣ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ይባላሉ) እነሱን ቀድሞ አውቃቸዋለሁ

በል እግዚእ የሀብከ ጽንአቶ ወይክስት ለከ አሜን

(በል ጌታ ፅናትን ይስጥህ ይግለፅልህም) (ይሁን ይደረግልኝ)

## ግሥ አርዕስት **(Root Verbs)**

የግሥ አርዕስት ማለት ለሌሎች ግሶች መሠረት በመሆን የሚከተሏቸው ግሶች የእነርሱን የአወራረድ ባህሪ የሚከተሉ እና በአቀማመጣቸው የሚመስሏቸው ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ግልፅ የሚሆኑት በዝርዝር ሥንመለከታቸው በመሆኑ በመጀመሪያ ግር ሊለን አይገባም፡፡ የሆነው ሆኖ ለግስ ርባታ መሠረት መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም፡፡ የታወቁት የግስ አርዕስታት ስምንት ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸውም የየራሳቸው ሠራዊት አላቸው፡፡

1. ቀተለ 3. ገብረ 5. ባረከ 7. ብህለ

2. ቀደሰ 4. አእመረ 6. ሤመ 8. ቆመ



www.debelo.org

## 6.1 እርባ ግስ (Tense and Nouns formation, including Adjectives)

በመጀመሪያ ግን አንድ በአንድ የስምንቱን ግሶች ቀለማት ብዛትና ዓይነት አንባቢው ማስተዋል ይገባዋል፡፡

1. ቀተለ ፍፁም ግእዝ ሆኖ የላላ
2. ቀደሰ ፍፁም ግእዝ ሆኖ የጠበቀ
3. ገብረ ግእዝ ሳድስ ግዕዝ ሆኖ የላላ
4. አእመረ ግእዝ ሳድስ ግዕዝ ሆኖ የላላ
5. ባረከ ራብዕ ግዕዝ ግዕዝ ሆኖ የላላ
6. ሤመ ኀምስ ግእዝ ሆኖ የላላ
7. ብህለ ሳድስ ሳድስ ግዕዝ ሆኖ የላላ
8. ቆመ ሳብዕ ግእዝ ሆኖ የላላ

ማንኛውም የቀዳማይ አንቀፅ ግስ ሁሉ ተነሽ መሆኑን በሥርዓተ ንባብ ላይ አይተናል፡፡

1. ቀተለ ---- ገደለ ( past tense - ሐላፊ ) / ቀዳማይ አንቀፅ /

   ይቀትል --- ይገድላል (future- ካልአይ --- ትንቢት ወይም Present Tense - የሁን ጊዜ)

   ይቅትል ---- ይገድል ዘንድ / ዘንድ አንቀፅ /

- ❖ ቀቲል / ቀቲሎት / -- መግደል / to kill ( infinitive) ንዑስ አንቀፅ /

  ቀታሊ -- የገደለ / ቅጽል --Adjective

  ቀታልያን --- የገደሉ /ወንዶች/ / ቅጽል ሲበዛ /

  ቀታሊተ --- የገደለች / ለሴት ቅጽል ሲሆን

  ቀታልያት --- የገደሉ / ለብዙ ሴቶች ቅጽል ሲሆን /

  ቅቱል ---- የተገደለ / ቅጽል -- Adjective/

  ቀታሊ ----ገዳይ / ስም ሲሆን /

  ቀትል --- ውጊያ / ጥሬ ዘር /

  ቅትለት --- አገዳደል / ሳቢዘር /

  በ **ቀተለ** ምሳሌ እንሰራና ሌሎችን እንዴት እንዳሚወርዱ ካየን በኋላ ሌሎችን በራሳችን መሥራት እንችላለን፡፡

  <u>ምሳሌ</u>፡

  አነ ቀተልኩ -- እኔ ገደልኩ

  አነ እቀትል --- እኔ እገድላለሁ

  አነ እቅትል --- እገድል ዘንድ/ ዘንድ አንቀፅ /

አነ እቅትል --- ልግደል /ትዕዛዝ/

አንተ ቀተልከ --- አንተ ገደልከ አንቲ ቀተልኪ---- ገደልሽ

አንተ ትቀትል --- አንተ ትገድላለሀ አንቲ ትቀትሊ--- ትገድያለሽ

አንተ ቅትል----- አንተ ግደል አንቲ ትቅትሊ ---- ትገድይ ዘንድ

ንሀነ ቀተልነ --- ገደልን አንቲ ቅትሊ --- ግደዬ

ንሀነ ንቀትል --- እንገድላለን አንትን ቀተልክን --- ገደላችሁ /ሴ/

ንሀነ ንቅትል --- እንገድል ዘንድ አንትን ትቀትል ---- ትገድላላችሁ / ሴ/

ንሀነ ንቅትል --- እንግደል አንትን ትቅትል---- ትገድሉ ዘንድ /ሴ/

አንትሙቀተልከሙ---ገደላችሁ /ወ/ አንትን ቅትል ---- ግደሉ /ሴ/

አንትሙትቀትሉ ----ትገድላላችሁ/ወ/ ውእቶሙቀተሉ --- ገደሉ /ወ/

አንትሙትቅትሉ ---ትገድሉ ዘንድ/ወ/ ውእቶሙይቀትሉ ----ይገድላሉ/ወ/

አንትሙቅትሉ ---- ግደሉ/ወ/ ውእቶሙይቅትሉ --- ይገድሉ ዘንድ/ወ/

ውእቱ ቀተለ --- ገደለ ውእቶሙይቅትሉ ---- ይግደሉ/ወ/

ውእቱ ይቀትል ----- ይገድላል ይእቲ ቀተለት ---- ገደለች

ውእቱ ይቅትል ---- ይገድል ዘንድ ይእቲ ትቀትል --- ትገድላለች

ውእቱ ይቅትል ---- ይግደል ይእቲ ትቅትል --- ትግደል ዘንድ / ሴ/

ውእቶን ቀተላ --- ገደሉ /ሴ/ ይእቲ ትቅትል--- ትግደል

ውእቶን ይቅትላ ---- ይገድላሉ /ሴ/

ውእቶን ይቅትላ --- ይገድሉ ዘንድ /ሴ/

ውእቶን ይቅትላ --- ይግደሉ /ሴ/

<u>ማስታወሻ</u>፣ ሀ. የትንቢት( future) እና የአሁን ጊዜ( Present) በግእዝ

አንድ ዓይነት የግሥ አወራረድ /አገባብ/ አላቸው፡ ፡

ለ. ዘንድ አንቀጽና ትዕዛዝ አንቀጽም እንዲሁ አንድ ዓይነት ናቸው፡ ፡

ሐ. የእግዝ ግሶች ርባታቸውን የሚጀምሩት በቀዳማይ አንቀጽ (past) ነው፡ ፡

**ቀተለ**ን የሚመስሉ ግሶች ነበረ፣ ወረደ፣ ወዘተ ናቸው፡ ፡ ነገር ግን አወራረዳቸው ከቀተለ ሊለዩ ስለሚችሉ ማስተዋል ያስፈልጋል ፡ ፡

<u>ምሳሌ</u> ወረደ፣ ይወርድ፣ ይረድ

2. ቀደሰ -- አመሰገነ | 3. ገብረ --- ሠራ፣ ፈጠረ

ይቄድስ --- ያመሰግን | ይገብር --- ይሠራል

ይቀድስ ---- ያመሰግን ዘንድ | ይግበር ---- ይሠራ ዘንድ

ይቀድስ ---- ያመሰግን | ይግበር ---- ይሥራ

❖ ቀድሶ /ቀድሶት/ --- ማመስገን | ገቢር /ገቢሮት/ --- መሥራት



www.debelo.org

ቀዳሲ ---- ያመሰግነ

ቀዳስያን ---- ያመሰግኑ

ቀዳሲት --- ያመሰግነች

ቀዳስያት --- ያመሰግኑ /ሴ/

ቅዱስ --- ምስጉን

ቀዳሲ --- አመስጋኝ

ቅዳሴ --- ምስጋና

መቅደስ --- ማመስገኛ

ቅድስት ---- የተመሰገነች

ገባሪ ---- የሠራ

ገባሪያን ---- የሠሩ

ገባሪት ---- የሠራች

ገባሪያት ---- የሠሩ /ሴ/

ግቡር ---- የተሠራ

ገባሪ ---- ሠሪ

ግብር ---- ሥራ

ግብረት ---- አሠራር /አደራረግ/

ምግባር ----- በጎ ሥራ

ተግባር --- ሥራ

እንደ ቀደሰ የሚረቡ ግሶች ሰብሐ፣ ጸለየ ናቸው፡ ፡

እንደ ገብረ የሚረቡ ግሶች ሠምረ፣ ኀብረ፣ ነጽሐ ወዘተ . . . ናቸው፡ ፡

4. አእመረ --- አወቀ

የአምር ---- ያውቃል

ያእምር ---- ያውቅ ዘንድ

ያእምር --- ይወቅ

❖ አእምሮ /አእምሮት/ --- ማወቅ

አእማሪ --- ያወቀ

አእማርያን --- ያወቁ /ወ/

አእማሪት --- ያወቀች

አእማርያት --- ያወቁ /ሴ/

እሙር --- የታወቀ

አእማሪ --- አዋቂ

ማእምር ---- የሚያውቅ

አእምሮ --- እውቀት

5. ባረከ --- ባረከ

ይባርክ --- ይባርካል

ይባርክ --- ይባርክ ዘንድ

ይባርክ --- ይባርክ

* ባርኮ /ባርኮት/ --- መባረክ

ባራኪ ---- የባረከ

ባራክያን --- የባረኩ

ባራኪት ---- የባረከች

ባራክያት --- የባረኩ /ሴ/

ቡሩክ --- የተባረከ

ባራኪ ---- የሚባርክ

ቡራኬ ----ቡራኬ

በረከት --- በረከት

❖ አእመረን የሚመስሉ፣ አጥረየ፣ አመንተወ፣ አመክነየ፣ አመድበለና የመሳሰሉት ናቸው፡ ፡

❖ እንደ ባረከ የሚረቡ ማህረከ፣ ፃመወ፣ ሳቀየ፣ ወዘተ . . . የመሳሰሉት ናቸው፡ ፡

6. ሤመ ---ሾመ

ይሠይም ---ይሾማል

7. ብህለ --- አለ

ይብህል --- ይላል



www.debelo.org

| | |
|---|---|
| ይሢም --- ይሾም ዘንድ | ይብሃል --- ይል ዘንድ |
| ይሢም ---- ያሹም | ይብሃል ---- ይበል |
| ❖ ሠይም /ሠይሞት/ --- መሾም | * ብሂል/ ብሂሎት/----ማለት |
| ሠያሚ --- የሾመ | ባህሊ---- ያለ |
| ሠያምያን --- የሾሙ | ባህልያን --- ያሉ |
| ሠያሚት --- የሾመች | ባህሊት --- ያለች |
| ሠያምያት --- የሾሙ/ሴ/ | ባህሊያት --- ያሉ /ሴ/ |
| ሥዩም ---- የተሾመ | ብሁል --- የተባለ |
| ሠያሚ ----ሿሚ | ባሃሊ ---- የሚል |
| ሢመት --- ሹመት | ባህል --- አባባል |

❖ ***ሤመ***ን የሚመስሉ ጌሰ፣ ዜነወ የመሳሰሉት ናቸው፡ ፡

❖ ***ብህለ***ን የሚመስሉ ጥቂቶቹ ውህዘ፣ ሥህወ፣ ጥዕየ ናቸው፡ ፡

8. **ቆመ --- ቆመ**

ይቀውም --- ይቆማል

ይቁም ----- ይቆም ዘንድ

ይቁም --- ይቁም

❖ ቀዊም/ ቀዊሞት/ --- መቆም

ቀዋሚ ---- የሚቆም

ቀዋምያን ---- የሚቆሙ

ቀዋሚት ----- የምትቆም

ቀዋምያት ---- የሚቆሙ/ሴ/

ቅውም --- የሚቆም

ቀዋሚ ---- ቋሚ

ቂመት ---- ቁመት

❖ **ቆመ**ን የሚመስል ሖረ፣ ሞርቅሐ /ላጠ/ ወዘተ . . . ናቸው፡ ፡

<u>ማስታወሻ</u>፣ የቆመ፣ የቆመች፣ ያመሰገኑ፣ ያመሰገነች የምንለው ግሡ በቀዳማይ / በሃላፊ/ ስለረባ እና ቅጽሎች እንደመሆናቸው ሁሉ "የ" የሚለውን ፊደል ለማመልከት ነው እንጂ ምን ጊዜም ለሃላፊ ወይም ለትንቢት ተብሎ ቅጽልን መከፋፈል አይደለም፡ ፡ ዘቆመት ስንልም ትርጉሙ ቀዋሚከሚለው ጋር አንድ ነው፡ ፡ የቆመች፣ ቋሚ ማለት ነውና፡ ፡

6.2 ሕገ ወጥ አካሄድ ያላቸው ግሶች፡ ፡ (Irregular Verbs)

<u>ቀዳማይ</u> <u>ካልአይ</u> <u>ዘንድ</u> <u>ትእዛዝ</u>



www.debelo.org

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወሀበ /ሰጠ/ | ይውህብ፣ ይሁብ | የሀብ | የሀብ |
| ክህለ /ቻለ/ | ይክል /ይክህል/ | ይክሀል | ይክሀል |
| ብህለ/አለ/ | ይብል | ይበል | ይበል |
| ይቤ /አለ/ | ይብል | ይበል | ይበል |
| ርእየ /አየ/ | ይርኢ | ይርአይ | ይርኢ /ይርእዩ/ |
| ወድቀ /ወደቀ/ | ይወድቅ | ይደቅ | ይደቅ |

❖ ድርጊቱ በመካሄድ ላለ ( Continuous)ነገር መጠቀም የምንችለው በካልአይ ነው

<u>ምሳሌ</u>፣ ይመጽእ ውእቱ

እንዘ ይመጽእ ውእቱ (እየመጣ ነው ሊመጣ ነው)

**7. አገባቦች (Prepositions and Conjunctions)**

**1.** <u>አቢይ አገባብ</u>፣ አገባቦች ማለት ብቻቸውን ሊነበቡ የማይችሉ መስተዋድዶች ናቸው፡ ፡ እነዚህም **እስመ**፣ **አምጣነ** ፣ **አኮኑ** / Since, because, for/ **እመ** /ቢሆንም/፣ **እስከ** ፣ **እንዘ** /ሲ፣ስ/**አመ**/ጊዜ/**ሶበ**/ጊዜ/ **አንተ**፣ **ዘ** ፣ **እለ** /የ/**ወ**/እና/የመሳሰሉት ናቸው፡ ፡

2.<u>ደቂቅ አገባብ</u>

**ውስተ** /ውስጥ/፣ **ምስለ** /ጋር/**ዓዲ** /ገና/፣ **እንከ** /ከንግዲህ/

3. <u>ንዑስ አገባብ</u>፣ **እም** /ን/፣ በ፣ ለ፣ ን

7.1 ግስ ላይ የሚያርÕ አገባቦች /ተስማሚ ቃላት/

ሀ. ከቀዳማይና ከካልአይ አንቀጽ ላይ ብቻ የሚያርፉ አገባቦች

<u>ምሳሌ</u> ሶበ፣ አመ፣ ጊዜ

ሶበ፣ ሰዓተ፣ ዕለት --- ጊዜ

እምጣነ ፣ አኮኑ፣ እስመ --- እና፣ ስለ

እንዘ

እመ

ዘ፣ እንተ

አምሳለ

ህየንተ

አርአያ

መጠነ

ከመ



www.debelo.org

ኀበ፣ መንግለ

ሶበ ተሰቅለ ክርስቶስ ጸልመ ፀሐይ ---ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ፀሐይ ጨለመ፡ ፡

ይወድቅ ይትነሳእ

ዛቲ ብእሲት እንተ ወለደት ወልደ እኅትየ ይእቲ

/ያቺ ወንድ ልጅ የወለደች ሴት እህቴ ናት/

አበውእለ መሀሩ ሃይማኖት ቅዱሳን ውእቶሙ

ተነበዩ ነቢያት ከመ ይትወለድ ክርስቶስ --ነቢያት ክርስቶስ እንዲወለድ ትንቢት ተናገሩ

አመ ይመጽእ ክርስቶስ በግርማ መንግስቱ ትርዕድ ምድር

ህየንተ ክብረ ጴጥሮስ ክብረ ጳውሎስ

ርእዩ መጠነ ገብረ ላቲ ተአምረ

ውእቱ ይስሐቅ እንዘ ትበኪ እህቱ

ያነግህ እንዘ ኢይነውም

እፎ ታነብብ እንዘ ኢትሜህር

እፎኑ ይከውን ሊተ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ

ኖመ ወልድየ አምጣነ ደከመ

ሰብሐ አቡየ ፈጥሪሁ አኮኑ ሰምዐ ጸሎቶ

ጸልመ ፀሐይ ሶበ ክርስቶስ ተሰቅለ

ጸልመ ፀሐይ አመ ክርስቶስ ተሰቅለ

ይትፌስሑ ጻድቃን አመ ክርስቶስ ይመጽእ

ተሐዝን እም አመ ወልዳ ይመውት

ዛቲ ብእሲት እንተ ወልደት ወልደ እኅትየ ይእቲ

አበውእለ ሃይማኖተ መሀሩ ቅዱሳን ውእቶሙ

አበውእለ በሌሊት ይተግሁ ይነውሙ በመዓልት

ርኢኩ ብእሴ እንዘ በጾም ይበልዕ

ውእቱ ይስሐቅ እንዘ እኅቱ ትበኪ

**ከዘንድ አንቀጽ ላይ የሚያርÕ አገባቦች እና ሌሎችም ከነዝርዝራቸው**

<u>ምሳሌ</u>

ከመ ---እንደ፣ ል፣ ዘንድ/ከዘንድ አንቀጽ ጋር/

እምቅድመ/አፍራሽ/ሳ/ሳይመጣ፣ ሳይሄድ፣ . . ./

እንበለ /አፍራሽ/ሳ/ሳይመጣ፣ ሳይሄድ

ሖረ ኀበ አሕዛብ ከመይንግር ምሕረቶ ለእግዚአብሔር አምላክነ



www.debelo.org

1. የእግዚአብሔርን ምሕረት እንዲነግር
2. የእግዚአብሔርን ምሕረት ሊነግር
3. የእግዚአብሔርን ምሕረት ይነግር ዘንድ

ጸልዩ ኀቤሁ ከመትረክቡ ዘትፈቅዱ

መኑ ውእቱ እግዚእ ከመንእመን ቦቱ

እምቅድመ ይትወለድ አብረሃም ሀሎኩ አነ

ነበረት ዘመናት ብዙኃት እንበለ ታእምር ረኀበ

አገባቦችን በመዘርዘር መጠቀም ይቻላል

1. እም-- ከ፣ እመኔየ ---በኔ፣ እምኔከሙ------ከእናንተ፣ እምኔሆሙ------ከእነሱ
2. ምሥለ --- ጋር፣ ምስሌየ ----ከኔ ጋር ፣ ምስሌከሙ----ከእናንተ ጋር፣ ምሥሌሆሙ------ ከነሡ ጋር
3. በእንተ-- ስለ፣ በእንቲአየ ----ስለእኔ፣ በእንቲአከሙ----ስለናንተ፣ በእንቲአሆሙ--- ስለእነሱ
4. ህየንተ --- ፈንታ /ስለ/፣ ህየንቴየ /ስለኔ ፈንታ/፣ ህየንቴከሙ/ስለ እናንተ/፣ ህየንቲአሆሙ/ስለእነሱ/

የሌሎች ተስማሚ ቃላት ትርጉማቸው

ወ --- እና

ወ --- ከግሡ ጋር የሚገባበት ጊዜ አለው፡ ፡ ምሳሌ ወሖረ፤ ነገር ግን ግሡን ይለውጠዋል ማለት አይደለም፡ ፡

ወ --- ም

ወ --- በሁለት ግሦች መሃል ሲገባ የነገሩን አወንታዊነት ይጠብቃል ወይም ያነለብታል፡ ፡

ምሳሌ፡ ተሰብአ ወተሠገወ /ተሠብአ ማለት ሰውሆነ /
/ተሠገወ ማለት ሰውሆነ /

ሂ --- ም/ እና

ኒ --- ትራስ ማለት የንባቡን ቃና ላለማበላሸት ምሳሌ ውእቱኒ

ኬ -- ውእቱኬ

ነገር ግን እንደ “ም”ሊሆኑ ይችላሉ፡ ፡

አይ፣ ምንት፣ ሚ፣ አ -- በምን ብሂል --- ማለት

ምንታት /አያት/ --- ምኖች በ --- በ

አይ --- ማናቸው ለ -- ን ፣ የ

አያት --- ማናቸው መ፣ ሂ፣ ኒ -- ም


www.debelo.org

አይቴ --- ወዴት    ዮም ---- ዛሬ

ማእዜ --- መቼ    ወትረ/ዘልፈ/ -- ሁልጊዜ

እፎ --- እንዴት    ዝየ --- በዚህ፣ በዚያ

በእፎ ---- ለምን    ህየ --- በዚህ፣ በዚያ

አሌ፣ አ፣ ወይ -- ወዮ    ናሁ፣ ነዋ -- እነሆ

ባሕቱ -- ነገር ግን

ነየ -- እነሆኝ

እመ፣ አመ--- ወይም    እስኩ -- እስኪ    እንጋ /

እንዳኢ/ -- እንጃ

ዕንቋዕ፣ ጥቀ --- ስንኳ    አመ፣ አሜን፣ አሜን -- አሜን

ሰ፣ ሳ፣ ስ --- ማ    ነዓ --- ና

ንስቲት፣ ሕዳጥ፣ ሕቀ ---ትንሽ    ሀብ፣ ህንባ -- እንካ

ጥቀ --- እጅግ    አንቢ ---- እምቢ

ፅሚተ --- ቀስ ብሎ    አንቋዕ --- እሰይ፣ አበጀ

ቅድም --- ፊት    ኩሉ --- ሁሉ

እንዘ ---- እየ፣ ሰ፣ ሳ፣ ስ    እመ -- ለ፣ ባ፣ ብ

ዳዕሙ----አላ፣    እንበለ --- ያለ፣ ሳይቀር

ባሕቱ -- እንጂ፣ ነገር ግን

**ዘ፣ እንተ፣ እለ፣ ለ** የተባሉት እነዚህ አገባቦች ዘርፍ አያያዥ ይባላሉ፡፡ ከ"ለ" ውጭ ያሉት ሦስቱ ዘርፍ ደፊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የዘርፍ ደፊም ሆነ የዘርፍ አያያዥ ዓላማ "የ" የሚል ትርጉምን ለማምጣት ነው፡፡

<u>ምሳሌ</u>፡ -

በ"ለ"ሲገኝ    በ"ዘ"ሲገኝ    በተናባቢ ሲገኝ    ወልዳ ለማርያም

ወልድ ዘማርያም    ወልደ ማርያም    (የማርያም ልጅ)

❖ በተናባቢ ጊዜ የተናባቢው መሪ የሚሆነው ቃል መድረሻው ሳድስ እንደሆነ /ወልድ/ ሳድሱ ወደ ግእዝ ይለወጣል፡፡ ይህ ሕግ ከተሳቢ ህግ የለየው ተሳቢው የሚጎላ ድምፅ ሲኖረው የተናባቢው መሪ የሚነሳ ድምፅ የሌለው በመሆኑ ነው፡፡ የተናባቢው መሪና ዘርፍ እንደ አንድ ቃል አብረው መነበብ አለባቸው በተናባቢ ጊዜ ዘርÕ ምንም ለውጥ አይደርስበትም፡፡

1. አብረሃም ብእሴ እግዚአብሔር ውእቱ

   መኑ ውእቱ ጸሐፌ ትእዛዝ ዘንጉሥ



www.debelo.org

2. ሕግ - በተናባቢ ጊዜ የተናባቢው መሪ የሚሆነው ቃል መድረሻው ሣልስ እንደሆነ /ብእሲ፣ ጸሐፊ፣ ወራሲ፣ ቀታሊ፣ ሰባኪ ወዘተ/

3. ሕግ - ሌሎች ቃላት የተናባቢ መሪ ሲሆኑ ምንም ዓይነት ለውጥ አይደርስባቸውም፡፡

| | ኢናባቢ |
|---|---|
| ደብተራ ዘኦሪት | ደብተራ ኦሪት |
| ሠረገላ ዘኤልያስ | ሠረገላ ኤልያስ |
| ዝማሬ ዘመላእክት | ዝማሬ መላእክት |
| ውዳሴ ዘማርያም | ውዳሴ ማርያም |
| ዶርሆ ዘመስተገብር | ዶርሆ መስተገብር |
| ከበሮ ዘማኅሌት | ከበሮ ማኅሌት |

| ዘርፍ አያያዥ | ዘርፍ ደፊ |
|---|---|
| ወልድ ዘዮሐንስ | ዘዮሐንስ ወልድ ትጉህ ውእቱ |
| ቤት ዘአቡየ ዐቢይ ውእቱ | ዘአቡየ ቤት ዐቢይ ውእቱ |

ዘርፍ አያያዦች በስምላይ

ምሳሌ፣ ወልድ ዘአቡነ እኁነ ውእቱ

እምእንተ ያዕቆብ

አኃት እለ ዚአየ ሠናይት አማንቱ

አኃት እለ የሁዳ የሐውራ ውስተ ቤተ ምኩራብ

አኃው ዘዮሴፍ ፈያታውያን ውእቶሙ

ግስ ላይ

❖ ተባእታይ ነጠላ

/በዚህ ጊዜ ጾታና ቁጥሩ እንደላይኛው ይጠብቃል /አገባቦቹ ዘ፣ እንተ፣ እለ የሚያርÕበት ግስ ግን ሁል ጊዜም ቀዳማይ አንቀጽ ወይም ካልአይ አንቀጽ መሆን አለበት፤ ሌሎች አንቀጾች ላይም አያርÕም፡፡ /

ወልድ ዘ፣ ወልድ ዘመጽአ፣ ወልድ ዘሞተ፣ ወልድ ዘይመጽእ፣ ወልድ ዘይመውት

ቤት ዘ፣ ቤት ዘተሐንጸ፣ ቤት ዘይትሐደስ

አብ ዘ፣ አብ ዘመሀረ ወንጌል፣ አብ ዘይዴሉ

እኁ ዘ፣ እኁ ዘያፈቅር እኁሆ፣ እኁ ዘይሜህር

❖ አንስታይ ነጠላ

ወለት 1. እንተ፣ ወለት እንተ ፈርሀት፣ ወለት እንተ ትሥሐቅ



www.debelo.org

2.ዘ፣ ወለት ዘፈርሀት፣ ወለት ዘትሥሕቅ

አዋልድ 1. እለ፣ አዋልድ እለ ይዘፍና፣ አዋልድ እለ ይሠንያ

ዘ፣ አዋልድ ዘይዘፍራ፣ አዋልድ ዘይገብራ

<u>ማስታወሻ</u> ሀ. "ዘ" የምንጠቀመው ለነጠላና ለብዙ ቁጥር ሲሆን፣ "እንተ"ግን ለነጠላ ቁጥር እንጂ ለብዙ አንጠቀምበትም፡፡ "እለ"ደግሞ ለነጠላ ቁጥር አይሆንም፡፡

ለ. "ለ"ብዙ ጊዜ የሚያገለግለው በተጠቃሽነት ነው፡፡

<u>ምሳሌ</u>፣ ቤታ ለሰሎሜ

ወልዱ ለአዳም

- ዘ -- ውእቱ

<u>ምሳሌ</u> ዘመጽአ --- የመጣ ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ስለዚህ ዘ ማሰሪያ ሊሆን ይችላል ማለት ነው፡፡

8. <u>**ተውሳከ ግስ ( Adverb)**</u>

ተውሳከ ግስ ማለት ግስን የሚያጎለምስ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በእንግሊዝኛው **I came <u>yesterday.</u> I will come <u>tomorrow</u>** የተሠመረባቸው ቃላት ተውሳከ ግሶች ናቸው፡፡ በግእዙ ትማልም/ትናንት/፣ ጌሰም/ነገ/እና ዘልፈ፣ ወትረ፣ ዮም ተውሳከ ግሶች ናቸው፡፡

<u>ምሳሌ</u> አነ እመጽእ ጌሰም

አንተ ትገይስ ወትረ ኀበ ቤተክርስቲያን

በግእዝ ቋንቋ ሳድስ የሆኑትን ቃላት በመለወጥ በ፣ ወደ፣ ከ የሚሉትን ቃላት ማምጣት ይቻላል፡፡

<u>ምሳሌ</u>

ዐርገ ሰማየ ወደ ሰማይ አረገ ዐርገ ውስተ ሰማይ

ወሖረ ብሔረ ወደ ሀገር ሄደ ወሖረ ኀበ ብሔሩ

ሖረት ብሔረ ርኁቀ ወደ እሩቅ ሀገር ሄደች ወሖረት ኀበ ብሔር ርኁቅ

<u>ማስታወሻ</u>

አንድ ቃል ከተለወጠ ከጎኑ ያለው ተስማሚው ቃል ይለወጣል፡፡

ስለዚህ የመጨረሻ ፊደሎችን በመቀየር ወደ፣ በ፣ ከ የሚል ትርጉም ልናመጣ እንችላለን ማለት ነው፡፡

<u>ምሳሌ</u> ሖረ ሀገረ-----ወደ ሀገር ሔደ

ሖረ ኀበ ሀገር

- ካዕብንም ወደ ሳብዕ በመቀየር **ወደ** የሚል ቃል ማምጣት እንችላለን፡፡



www.debelo.org

ምሳሌ ቤቱ፣ ቤቶ፣ ወሖረ ቤቶ፣ ወደ ቤቱ ሄደ፡ ፡

ስለዚህ የሚከተሉትን በደንብ ለመገንዘብ እንሞክር፡ ፡

ወአኀዙ ኪያሁ ይእተ ሰዓተ ------ ወአኀዙ ኪያሁ በይእቲ ሰዓት

ይገብር ግብሮ መዓልተ ወሌሊተ ---- ይገብር ግብሮ በመዓልት ወበሌሊት

ጸሊ ኀበ አቡከ ሰማያዊ ኅቡአ ---- ጸሊ ኀበ አቡከ ሰማያዊ በኅቡእ

ውእቱ ሖረ ቤቶ ------ ውእቱ ሖረ ኀበ ቤቱ

ወእንዘ ይነብር ዐውደ ---- ወእንዘ ይነብር በዐውድ

**9.** አሉታ

በግእዝ ቋንቋ አነጋገር አፍራሽ የሚሆኑ ፊደሎች አልቦ፣ ኢ፣ አኮ፣ ሐሰ፣ ናቸው፡ ፡ አልቦ /“ N0” ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ተመሳሳይ ነው/ ትርጉመም የለም ማለት ነው፡ ፡

ቦ -- አለ ፤ አልቦ -- የለም

ምሳሌ ሀ . አልቦ ዘመድ በጊዜ መከራ --- በመከራ ጊዜ ዘመድ የለም

ለ . አልቦ ብእሲ ዘይታመን በዘመንነ ---- በዘመናችን የሚታመን ሰው የለም

ሐ. ለእሉ ነዳያን አልቦሙ ዘመድ --- ለነዚያ ድሆች ዘመድ የላቸውም

መ. ርኅቡ ሕጻናት ወአልቦ ዘይበልዑ --- ህፃናት ተራቡ የሚበሉትም የለም

ሠ. አልብየ ዘመድ ዘ እንበለ እግዚአብሔር --- ያለ እግዚአብሔር ዘመድ የለኝም

ረ . አልባቲ ውሉድ ለዛቲ ብእሲት --- ለዚች ሴት ልጆች የሏትም

ኢ /አሉታ/

ሀ . ኢተመየጠ አቡየ እምዘሖረ --- አባቴ ከሔደ አልተመለሰም

ለ . ዘሕመም ብእሲ ኢበልዐ እክለ ወኢሰትየ --- የታመመው ሰው እህል አልበላም፤ አልጠጣም

ሐ. ዕቡይ ገብር ኢይምጻእ ኀቤየ

መ. ገበርኩ ዘንተ በኢያእምሮ

ሠ . ኢታፍቅሩ ወርቀ ወ ኢብሩረ ሰብአ ዓለም

ረ . ኢመላክ ወኢነቢይ በሳማናዊት ዘመን

አኮ ሀ . አኮ አነ ዘገበርኩ ዘንተ ግብረ

ለ . አኮ ፍቁርየ ሰይጣን አላ ፀርየ

ሐ. ዝንቱ ረድእ አኮ ትጉህ

መ. አኮ ነቢይ ዘወረደ እምሰማይ አላ ወልደ አብ

ምልማድ / መልመጃ /

በአወንታ የተፃፉትን ዐረፍተ ነገሮች ወደ አፍራሽ ለውጥ



www.debelo.org

ሀ.ቦ ሰላም በዘመንነ

ለ.ቦ ኤልያስ ሕይወት ዘያስትፌስሕ

ሐ.ቦ ደቂቅ ለእምየ

ወደ ግእዝ መልስ /ወልጥ /ሚጥ/ ኀበ ልሳነ ግእዝ/

1. ብዙ በመሄድ ደከምኩ
2. አጆቼን ለጸሎት ወደ አንተ እዘረጋለሁ
3. ወደ አንተ በጮኹ ጊዜ ስማ
4. ይህን ያህል የምታስብለት ማን ነው
5. እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ከሆነ ችግር የለም
6. ድንግል ከግብፅ ተመለሰች

ወደ አማርኛ መልስ /ወልጥ ኀበ ልሳነ አምሀራ/

1. ወለደቶ ማርያም እንዘ ድንግል ይእቲ
2. ወአጽገቦሙ እምበረከቱ ለርኁባን
3. ስብሐት ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ
4. ኀደረ ላዕሌኪ ለመድኃኒተ ዚአነ

አገባቦችን እየተጠቀምክ በእነዚህ አማካኝነት ዐረፍተ ነገር ሥራ /ግበር ዐረፍተ ነገር/

| | |
|---|---|
| ሐለየ /አሰበ/ | ረገመ /ረገመ/ |
| ምሴት /ምሽት/ | ተወከለ /ታመነ / |
| ረድአ /ረዳ | ነዳይ /ደሀ/ |
| በከየ /አለቀሰ/ | ባዕል /ሀብታም/ |
| ተለወ /ተከተለ/ | ንዋይ /ገንዘብ/ |
| ክሳድ/አንገት/ | ከልብ /ውሻ/ |
| እዝን /ጆሮ/ | አጥረየ /ገዛ/ |
| ስን /ጥርስ/ | ጌሠ/ገሠገሠ/ |
| ንዋም /እንቅልፍ/ | ደቂቅ /ሕፃን ልጅ/ |
| ሰከበ/ተኛ/ | ገነየ /አመሠገነ / |
| ሰዐመ/ ሳመ/ | ቦ /አለ/ |
| እለ/እነ / | ዲበ /ላይ/ |
| ህየ /እዚያ/ | ወድቀ /ወደቀ/ |
| ዝየ /በዚህ/ | ጥቀ/ በጣም/ |
| ምስያጥ /ገበያ/ | ገብዐ /ገባ/ |

ሓራ /ወታደር፣ ጭፍራ፣ /ነጠላ፣ ብዙ/



www.debelo.org

በቅንፍ ውስጥ ያለውን ግስ በቀዳማይ፣ በካልአይ፣ በዘንድ አንቀጽ በሚገባው ሁሉ አስተካክለውና ትርጉም ስጥ/ስጭ/ ሀብ ትርጓሜሆሙለእሉ አናቅፅ/

<u>ምሳሌ</u>፣ ከመ/ቀደሰ/ 1. ከመ ቀደሰ --እንዳመሰገነ

2.ከመ ይቄድስ ---እንደሚያመሰግን

3. ከመ ይቀድስ ----ያመሰግን ዘንድ፣ ቢያመሰግን፣ እንዲያመሰግን

| | |
|---|---|
| ከመ/ተሰቅለ/ | ሶበ /ተሰቅለ/ |
| አመ/ሰምዐት/ | አምጣነ /ገብራ/ |
| ሶበ /መጽአ/ | አምጣነ/አከብርከሙ/ |
| እምቅድመ/ተወልዳ/ | እስመ/ፈፀምከ/ |
| ከመ/አእመርነ/ | እስመ/ሰማዕነ/ |
| እንበለ/በላእነ/ | እንተ/አፍቀረ/ |
| እንበለ /ሰምዐት/ | እለ /ጸለዩ/ |
| ዘ/ተቀብረ/ | እለ /ዜነዋ/ |
| እንዘ/በላዕከ/ | እመ/ነበርኪ/ |
| ከመ/አመንኪ/ | አመ/ገበርከን/ |

ለሚከተሉት ግሶች በካልአይ እና በትዕዛዝ አስቀምጥ/አንብር ለእሉ አናቅጽ በካልአይ ወበትዕዛዝ/

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ነበረ | 3. ነጸረ | 5. ሖረ | 7. ምዕዘ |
| 2. ሰብሐ | 4. ተንበለ | 6. ዜነወ | 8. ወድቀ |

<u>ንግግር</u>

| | |
|---|---|
| ሰላም ለከ ወልድየ | እግዚአብሔር ይሴባሕ ወሰላም ለከ አቡየ |
| ሰላም ላንተ ይሁን ልጄ | እግዚአብሔር ይመስገን ላንተም ሰላም አባቴ |
| አብያጺከ፣ ሰብአ ቤትከ ዳኅና ውእቶሙ | እወ አቡየ ሎቱ ስብሐት |
| ጓደኞችህ፣ ቤተሰቦችህ ደህና ናቸው | አወ አባቴ ለእርሱ ምስጋና |
| መጽሐፈ ጸሎት ብከ | በአማን |
| የጸሎት መጽሐፍ አለህ | በእውነት |
| ልሳነ ግእዝ እፎ ውእቱ | ቀሊል ውእቱ |
| የግእዝ ቋንቋ እንዴት ነው | ቀላል ነው |
| ናሁ ትትናገር ጥቀ | ንስቲት ንስቲት |
| አሁን በጣም ትናገራለህ | ትንሽ፣ ትንሽ |
| ባሕቱ ምንት ይገብር ለከ | ይትሔደስ መንፈስየ አመሰማእኩ በእዝንየ ልሳነ ግእዝ |



www.debelo.org

ነገር ግን ምን ያደርግልሀል   የግእዝ ቋንቋ በሰማሁ ጊዜ መንፈሴ ይታደሳል

| | |
|---|---|
| እንከሰ ኩሉ ሰብእ እመይትናገር ሠናይ ውእቱ | ተስፋየ ውእቱ |
| እንግዲስ ሁሉ ሰውቢናገረውጥሩ ነው | ተስፋየ ነው |
| ናሁ እለመኑ ይትናገሩ ልሳነ ግእዝ | ብዙኃን ውእቶሙአኮ አነ ባሕቲትየ |
| አሁን እነማን የግእዝ ቋንቋን ይናገራሉ | ብዙዎች ናቸውእኔ ብቻ አይደለሁም |
| ምንት ትቤ አንተ እንዘ ይትናገሩ ልሳነ ግእዝ | ፍስሐ ፈድፈደ ሊተ |
| ግእዝ ሲናገሩ አንተ ምን ትላለህ | ደስታ በዛልኝ |
| ማዕዜ ውእቱ ዘወጠኑ ለምሂር | በዝንቱ አመት |
| መቼ ነውለመማር የጀመሩ | በዚህ አመት |
| እግዚአብሔር ያርእየነ ለፍሬሁ | አሜን ለይኩን |
| እግዚአብሔር ፍሬውን ያሳየን | አሜን ይሁንልን |

## አገናዛቢ አጸፋዎችና (Possessives) ስሞች

አገናዛቢ አጸፋዎች በስም መድረሻ እያረፉ ስሙየ ሚመለከተውነገር ለማን እንደሆነ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ምሳሌ፡-እናቴ፣ እናትህ፣ እናቱ፣ እናቷ ...

በዓረፍተ ነገር፡-

ማርያም ድንግል አምነ ይእቲ

ወልድኪ አድኅነ ዓለመ

አይቴ ተሰቅለ ወልዳ

ወልድየ ትጉህ ውእቱ

በቃላት እም፣ ጸሎት እና ቅዳሴ የሚባሉት ስሞች እንዴት እንደሚለወጡ ተመልከት፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| አነ | እምየ /እናቴ/ | ጸሎትየ | ቅዳሴየ |
| አንተ | እምከ | ጸሎትከ | ቅዳሴከ |
| አንቲ | እምኪ | ጸሎትኪ | ቅዳሴኪ |
| ውእቱ | እሙ | ጸሎቱ | ቅዳሴሁ |
| ይእቲ | እማ | ጸሎታ | ቅዳሴሃ |
| አንትሙ | እምክሙ | ጸሎትክሙ | ቅዳሴክሙ |
| ንሕነ | እምነ | ጸሎትነ | ቅዳሴነ |
| አንትን | እምክን | ጸሎትክን | ቅዳሴክን |
| ውእቶሙ | እሞሙ | ጸሎቶሙ | ቅዳሴሆሙ |


www.debelo.org

ውእቶን እሞን ጸሎቶን ቅዳሴሆን

**ማስታወሻ**

የቃሉ መጨረሻ ፊደል ሳድስ ካልሆነ ሁ፣ ሃ ይላል፡፡ ቅዳሴሁ፣ ቅዳሴሃ እንዲል፡፡

የቃሉ መጨረሻ ፊደል ሳድስ ከሆነ ፊደሉን ለጊዜው መቀየር ነው“ ጸሎቱ፣ ጸሎታ

- ❖ እንዲህ የሚሆነው ግን በስም ብቻ ነው፡፡ በመስተዋድዶች ላይሆን ይችላል፡፡

አገባቦች/መስተዋድዶች/እንዴት እንደሚለወጡ፣ ኀበ = ወደ፤ ዲበ =ላይ . . .

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኀቤየ /ወደእኔ/ | ላዕሌየ /በላይ/ | ከማየ /እንደኔ/ | ታህቴየ |
| ኀቤከ | ላዕሌከ | ከማከ | ታህቴከ |
| ኀቤኪ | ላዕሌኪ | ከማኪ | ታህቴኪ |
| ኀቤሁ | ላዕሌሁ | ከማሁ | ታህቴሁ |
| ኀቤሃ | ላዕሌሃ | ከማሃ | ታህቴሃ |
| ኀቤነ | ላዕሌነ | ከማነ | ታህቴነ |
| ኀቤከሙ | ላዕሌከሙ | ከማከሙ | ታህቴከሙ |
| ኀቤከን | ላዕሌከን | ከማከን | ታህቴከን |
| ኀቤሆሙ | ላዕሌሆሙ | ከማሆሙ | ታህቴሆሙ |
| ኀቤሆን | ላዕሌሆን | ከማሆን | ታህቴሆን |

### 1ዐ.1 አገናዛቢ ተውላጠ ስሞች

/የኔ፣ ያንተ፣ ያንቺ፣ የናንተ . . ./

1. ዚአየ /እኔ/፣ የኔ፣ የኔው
2. እንቲአየ /እኔ/፣ የኔ፣ የኔዋ፣ የኔይቱ
3. እሊአየ /እኔ/፣ የኔ፣ የኔዎቹ

| | | | |
|---|---|---|---|
| አነ | ዚአየ | እንቲአየ | እሊአየ |
| አንተ | ዚአከ | እንቲአከ | እሊአከ |
| አንቲ | ዚአኪ | እንቲአኪ | እሊአኪ |
| ውእቱ | ዚአሁ | እንቲአሁ | እሊአሁ |
| ይእቲ | ዚአሃ | እንቲአሃ | እሊአሃ |
| ንሕነ | ዚአነ | እንቲአነ | እሊአነ |
| አንትሙ | ዚአከሙ | እንቲአከሙ | እሊአከሙ |
| አንትን | ዚአከን | እንቲአከን | እሊአከን |



www.debelo.org

ውእቶሙ ዚአሆሙ እንቲአሆሙ እሊአሆሙ

ውእቶን ዚአሆን እንቲአሆን እሊአሆን

ምሳሌ 1፡ -በተናባቢ

- እመዚአየ፣ የእኔ እናት፣
- አበዚአከሙ፣ የእናንተ አባት

ምሳሌ 2፡ -በ ዘ ሲያያዝ

- ሐመር ዘዚአነ፣ የእኛ መርከብ
- አበው ዘዚአነ አብርሃም ወይስሐቅ ውእቶሙ፣ የእኛ አባቶች አብርሃምና ይስሐቅ ናቸው፡ ፡

**ማስታወሻ** የዚአየ፣ እንቲአየ፣ እሊአየ ምንጫቸው ዘ፣ እንተ፣ እለ ከሚሉት ነው፡ ፡ ስለዚህ የአገናዛቢዎችን ሙያ ለመለየት ወደኋላ በመመለስ የዘ፣ እንተ፣ እለ ሙያቸው ምን እንደሆነ መለየት አለብን፡ ፡

“ዘ”ለብዙም፣ ለነጠላም

“እለ”ለብዙ

“እንተ”ለነጠላ

ዘ፣ አለ፣ አንተ፣ =የ

## 1.2 የአንዳንድ አገናዛቢ አፀፋዎች ዝርዝር

ካልእ =ሌላ፣ ካልእከ /ሌላህ/ካልእኪ የሌላሽን

ቀደምት =/የቀድሞ ሰዎች/፣ ቀደምትከሙ/የቀድሞ ሰዎች የሆናችሁ እናንተ/

ክልኤ = ሁለት፣ ክልኤሆሙ/ሁለታቸው/፣ ክልኤነ /ሁለታችን /ክልኤከሙ/ሁለታችሁ/

በበይናት = ( ከ ተየበይን ቤቱ /በመካከል እርስ በርስ

በበይናት/እርስበርሳችን /በበይናቲሆሙ/እርስ በርሳቸው/በበይናቲከሙ/እርስ በርሳችሁ/

ኩሎ = ሁሉ፣ ኩሎሙ/ሁላቸው/ /ኩልከመ/ /ሁላችሁ/ኩልነ /ሁላችን/

ባሕቲት = ብቻ፣ ባሕቲቶሙ/ብቻቸውን/፣ ባሕቲትየ /ብቻየን/፣ ባሐቲታ /ብቻዋን/

አመ = ጊዜ፣ አሜሃ /በዚህ ጊዜ፣ በዚያ፣ ጊዜ፣ ወዲያው/

ሶበ = ጊዜ፣ ሶቤሃ /በዚህ ጊዜ፣ በዚያ ጊዜ፣ ወዲያው/

ጊዜ =ጊዜ፣ ጊዜሃ /በዚህ ጊዜ በዚያ ጊዜ ወዲያው/

ምሳሌ



www.debelo.org

ዘትፈቅድ ለርእስከ ግበር ለካልእከ = ለራስህ የምትፈልገው ለሌላው አድርግ፡፡

ሰማእክሙ ዘተብህለ ለቀደምትክሙ/ተብህለ = ተባለ/

ቀደምትክሙ ሰገዱ ለእግዚአብሔር አምላኮሙ

ክልኤሆሙ ሖሩ ወብልዑ ኅብስተክሙ

ተፋቀሩ በበይናቲክሙ

ተማከርነ በበይናቲነ

ተሰአሉ በበይናቲሆሙ/ተሰአለ፣ ተጠያየቀ/

ኩልነ አግብርተ እግዚአብሔር ንሕነ

መጽኡ ኩሎሙ ወሰአሉ በእንተ ንጉሦሙ

ሖሩ ኩልክሙ ኀበ ቤትክሙ ለክሙ

ኩሎሙ ነቢያት አስከ ዮሐንስ ተንበዩ

መጻእኩ እምብሔር ርኁቅ ባሕቲትየ

ዝንቱ ብእሲ ነበረ ውስተ ቤቱ ለባሕቲቱ

ዘበልዐ ባሕቲቶ ይመውት ባሕቲቶ

<u>የንዑስ አንቀጽ ዝርዝር እንደ አገናዛቢ ሲያገለግል</u>

ቀቲል/ቀቲሎት/ --መግደል ቀቲልየ = መግደሌ ቀቲልክሙ= መግደላችሁ

ቀተለ = ገደለ ቀቲሎትየ = መግደሌ ቀቲሎትክሙ= መግደላችሁ

ቀደሰ = አመሰገነ ቀድሶየ = ምስጋናየ ቀደሶክሙ= ማመስገናችሁ

ገቢር/ገቢሮት/=መሥራት ቀድሶትየ = ምስጋናየ ቀድሶትክሙ= ማመስገናችሁ

ገብረ = ሥራ ገቢርየ = ሥራየ ገቢርክሙ= ሥራችሁ

ገቢሮትየ = ሥራየ ገቢሮትክሙ= ሥራችሁ

**1ዐ .3 ተጠቃሽ ተውላጠ ሥም**

| <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> |
|---|---|
| ሊተ = የእኔ ፣ ለእኔ ፣ ልኝ | ለነ = ለእኛ |
| ለከ = ላንተ፣ ልህ | ለክሙ= ለእናንተ ላቸሁ |
| ለኪ = ላንቺ፣ ልሽ | ለክን = ለእናንተ /ለሴት/ላቹሁ |
| ሎቱ/ሎ/ = ል፣ እርሱ | ሎቶ/ሎቶመ/ሎሙ= ለእነርሱ /ለሴት/ |
| ብየ = በኔ፣ ብኝ፣ አለኝ | ብነ = በእኛ ብን አለን |
| ብከ = በአንተ፣ አለህ | ብክሙ= በእናንተ፣ ባችሁ ፣ አላችሁ |
| ብኪ = በአንቺ አለሽ | ብክን= በእናንተ፣ ባችሁ አላቹሁ |
| ቦቱ/ቦ/= በት አለው፣ በእርሱ | ቦኑ/ቦቶመ/ = አላቸው፣ አላችህ ባቸው/ |



www.debelo.org

ባቲ/ባ/= ባት

ቦን /ቦቶን/= አላቸው፣ አላችህ፣ ባቸው

ላቲ=ለእርሷ

ሎሙ= ለእነርሱ /ለወንዶች/፣ ባቸው

<u>ምሳሌ</u>

ፍታህ ሊተ ወተበቀል በቀልየ

ልበ ንፁሐ ፍጥር ሊተ

ሰላም ለከ ኦ ሚካኤል መልአከ አድኅኖ

ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ

ሎቱ ስብሐት

አምጽኡ ላቲ አምሐ ለድንግል

ብየ እግዚአብሔር ዘየዐቀበኒ

መጻእ ብየ ሞት አመነበርኩ በኃጢአት

ኦ ኅልያድ አይቴኑ ትበውእ እስመ በጽሐ ብከ ዳዊት

ብኪ ግርማ ራእይ ዘየዐቢ

ወተቀትለ ባቲ ወልዳ ለአዳም

ወተሰቅለ ባቲ ወልዳ ለማርያም

ተአገሠ ለነ ኩሎ ኃጢያተነ

ሰአሊ ለነ ቅድስት

ሰላም በከሙ

## 1ዐ .4 ቦ /አለ/ በመራሕያን ሲረባ / Verb to have/

ብየ = አለኝ <u>ምሳሌ</u> ምንት ብየ ምስሌኪ ካንቺ ጋር ምን አለኝ

ብከ=አለህ ምንት ብከ ምስሌሃ ከርሷ ጋር ምን አለህ

ብኪ = አለሽ ምንት ብኪ ምስሌሃ ከርሷ ጋር ምን አለሽ

ብነ = አለን ምንት ብነ ምስሌከሙ ከእናንተ ጋር ምን አለን

ብከሙ=አላችሁ ምንት ብከሙምስሌሆሙ ከእነርሱ/ከሴቶች/ጋር ምን አላችሁ

ብከን=አላችሁ /ለሴት/ ምንት ቦሙምስሌየ ከእኔ ጋር ምን አላቸው

ቦሙ= አላቸው ምንት ቦሙምስሌየ ከእኔ ጋር ምን አላቸው

ቦን = አላቸው/ለሴት/ ምንት ቦን ምስሌኪ ከአንቺ ጋር ምን አላቸው

ከላይ ለጠቀስናቸው አፍራሻቸው አል ነው፡ ፡ <u>ለምሳሌ</u> አልብየ = የለኝም

አልብከ = የለህም

አልብኪ = የለሽም

አልብነ = የለንም



www.debelo.org

አልቦ = የለንም፣ የሉም፣ የለም

ቦ = አለ ፣ አለው

ዘቦ = ያለው

## 10.5 ባለቤት ተውላጠ ስም (Subjective Pronoun)

እግዚአብሔር ለሊሁ ፈጠረ ዓለመ /እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ዓለምን ፈጠረ/

ለሊሁ አእምር

ለሊከ እግዚኦ ተአምር አበድየ

ለሊከ እግዚኦ ተአምር ጽእለትየ

ለሊከሰ ሕይወተ ተሐዩ

ለሊኪ አውሰብኪ

ለሊሃ ትበልዕ ኩሎ ዘትረክብ

ትአምሩ ለሊክሙ ኩሎ ነገር ዘኮነ በይሁዳ

ለሊሁሰ እግዚእ ኢየሱስ ኢያጥመቀ ዳእሙ አርዳኢሁ/ ዳእሙ-- እንጂ/

| __ነጠላ__ | __ብዙ__ |
|---|---|
| ለሊሁ= እርሱ እራሱ / Himself/ | ለሊሆሙ= እነርሱ እራሳቸው (Themselves) |
| ለሊሃ = እርሷ እራሷ (Herself) | ለሊሆን = እነርሱ /ለሴት/ (Themselves) |
| ለሊከ = አንተ እራስህ (Yourself) | ለሊክሙ= እናንተ እራሳችሁ ( Yourselves) |
| ለሊኪ=አንቺ እራስሽ (Yourself) | ለሊክን = እናንተ እራሳችሁ /ለሴት/ ( Yourselves) |
| ለሊየ /ለልየ = እኔ እራሴ/ ( My self) | ለሊነ = እኛ እራሳችን ( 0urselves) |

## 10.6 ተሳቢ ተውላጠ ስሞች ( Objective Pronouns)

| __ነጠላ__ | __ብዙ__ |
|---|---|
| ኪያየ = እኔን ( Me) | ኪያነ = እኛን (Us) |
| ኪያከ = አንተን ( You) | ኪያክሙ=እናንተን (You) |
| ኪያኪ = አንቺን ( You) | ኪያክን =እናንተን ( You) ለሴት |
| ኪያሁ= እሱን ( Him) | ኪያሆሙ=እነርሱን ( Them) |
| ኪያሃ =እሷን ( Her) | ኪያሆን = እነርሱን ( Them ለሴት/ |

__ምሳሌ__



www.debelo.org

ዘርእየ ኪያየ ርእየ አቡየ

መኑ ይጼውእ ኪያከ

ኪያከ ሰናይተ ዘፈጠረ እግዚአብሔር ይትባረከ

ቀድሱ ኪያሁ ወባርኩ ስሞ

አምላክነ አድኅነ ኪያነ እምሞት

ዘተወከፈ ኪያከሙተወከፈ ኪያየ

ፈኑ ኪያሆሙኅበ አሕዛብ

ርእየ ኪያክን ወተፈስሐ ብክን

→ ስለዚህ ተሳቢ ማለት "ን" የሚለውን ቃል ወይም ፊደል የሚያመጣ ማለት ነው፡ ፡

**<u>የማየበዙ ፊደላት</u>**

አ፡ -

| <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> | <u>የብዙ ብዙ</u> |
|---|---|---|
| ደብር | አድባር | አድባራት |
| ርእስ | አርእስት | |

ከዚህ ላይ የቃላቱን መጨረሻ ሁለት ፊደላት ማስተዋል ነው፡ ፡ ብር፣ እስ /ሳድስ ናቸው፡ ፡ /

ን፡ - ሀ . ደራሲ +ያን =ደራስያን

ሠዓሊ +ያን =ሠዓልያን

ለ . ኢትዮጵያዊ +ያን = ኢትዮጵያውያን

ሐ. ቅዱስ =ቅዱሳን

ብፁዕ = ብፁዓን

መዘምር =መዘምራን

ከዚህ ላይ የቃላቱ የመጨረሻው ሁለት ፊደላት ራብዕና ሣልስ ናቸው፡ ፡ ራሲ፣ ዓሊ፣ እንደገና የመጨረሻዎቹ ሁለት ፊደላት ፁዕና ዱስ ይላል፡ ፡

ት፡ - ኢትዮጵያዊት + ያት - ኢትዮጵያውያት

ሰማይ =ሰማያት

ቅድስት =ቅዱሳት

ሠናይት =ሠናያት

❖ አሁንም ቢሆን የቃላቱን ሁኔታ ማስተዋል ነው፡ ፡

መ፡ - ኩሉ -- ኩሎሙ ለሊሁ -- ለሊሆሙ እ፡ - ኃጢአት -- ኃጣውእ

አንተ -- አንትሙ ለሊከ -- ለሊከሙ



www.debelo.org

ይ፡ -መርዔት= መራዕይ

ሌሊት = ሌያልይ

ው፡ -ዕፅ = ዕፀው

አብ = አበው

እድ = እደው

ል፡ -ኪሩብ = ኪሩቤል

<u>የጸያፍ አበዛዝ ምሳሌ</u>

መምህራን፡ መምህራኖች

ደራሲያን ፡ ደራስያኖች

ቅዱሳን ፡ ቅዱሳኖች

ወልጥ ሀበ ልሳነ አምሀራ /ወደ አማርኛ ለውጥ/

1. እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ
2. መንፈስ ቅዱስ ኃደረ ላእሌኪ
3. አአትብ ገጽየ ወኩለንታየ በትእምርተ መስቀል
4. አዋልደ እሊአከ ወውሉደ እሊአየ ይትፋቀሩ በበይናቲሆሙ
5. ይቤ ክርስቶስ በአፈ ነቢይ ተካፈሉ አልባስየ
6. አርድእተ እሊአሁ ይተግሁ ለአንብቦ መጻሕፍት
7. ዘዚአነ አምላክ መሀሪ ውእቱ
8. ለነ አበዊነ መሀሩ ሀይማኖቶሙ
9. ኢያፈቅር አንሰ እለ ይሰክሩ በወይን
10. ጸሎታ ለማርያም ያድኅን እምመአተ ወልዳ
11. ሰብእ እንተ ኢኮነ ጻድቅ
12. አንተ ውእቱ ወልድ ዘ ቤተክርስቲያን
13. አ አባ ሥረይ ሎሙ ኃጢአቶሙ
14. አሜሃ ያቀውም አባግዐ በየማኑ ወአጣሌ በፀጋሙ
15. ወአውረደ ሎሙ እምሰማያት
16. ኪዳነ ተወከሉ አበዊነ ወኢትኃፍሩ
17. ኅደረ ላእሌኪ ለመድኃኒተ ዚአነ
18. ፍታሕ ሊተ ወተበቀል በቀልየ
19. ሰላም ለከሙ አኃውየ
20. ብኪ ድኅነ ዓለም ወበወልድኪ ኮነ ሰላም
21. አክብሩ እምነ ማርያምሃ እስመ አልባቲ መስና
22. አንቲ ውእቱ እፅ ዘርእየ ሙሴ
23. ነዋ ወልድኪ ወነየ እምከ
24. አልቦ ነገር ዘይሰዐኖ ለእግዚአብሔር



www.debelo.org

25. ዘቦ እዝን ሰሚአ ለይስማዕ

26. ያስተበቁዕ ኀበ እግዚአብሔር

27. አይልሳን ዘይክል ነቢበ ዘይትናገር በእንቲአኪ

**እለ ፣ እንተ እና ለ ን በመጠቀም ባዶ ቦታውን ሙላ**

<u>ምሳሌ</u> ወልድ ዘ

ብእሲ እንተ

አበው እለ

አቡሁ ለ

| | |
|---|---|
| 1. መምህር | 9. ደናግል |
| 2. ሞት | 10. ኖላዊ |
| 3. መንበር | 11. አኀው |
